አንድም በኔ ላይ ሰላምታን የሚያቀርብ የለም ለርሱ ሰላምታን እስክመልስ ድረስ አላህ ለኔ ነፍሴን የሚመልስልኝ ቢሆን እንጂ።

ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: የአላህ መልክተኛ (ሶለሏሁ ዐለይሂ
ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ብለዋል: "አንድም በኔ ላይ ሰላምታን የሚያቀርብ የለም ለርሱ
ሰላምታን እስክመልስ ድረስ አላህ ለኔ ነፍሴን የሚመልስልኝ ቢሆን እንጂ።" [ሰነዱ ሐሰን ነው።] [አቡዳውድና አሕመድ ዘግበውታል።]

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ከቅርብም ይሁን ከሩቅ ሆኖ በርሳቸው ላይ ሰላምታን ባቀረበ ሁሉ ላይ ሰላምታን ሊመልሱ ዘንድ ነፍሳቸው እንደምትመለስላቸው ተናገሩ። የቀብርና የበርዘኽ ህይወት የሩቅ ጉዳይ ነው። ከአላህ በቀርም እውነታውን የሚያውቅ የለም። እርሱም በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/6222